የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 7/2004

ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ባህር ዳር

ጥር

2004 ዓ.ም.

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 7/2004

1. አውጭው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2004 አንቀጽ 67 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 7/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ...../2004 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. "ዕቃና አገልግሎት" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለንብረተሰቡ በቋሚነት የሚያቀርቡት ዕቃ፣ የሚሰጡት አገልግሎት እና የሚያዘጋጁት መገልገያ ነው።
2. "ሙሉ ኢኮኖሚያዊ ወጪ" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሕብረተሰቡ በቋሚነት ለሚያቀርቡት ዕቃና ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያደርጓቸው ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ነው።

4. የተፈፃሚነት ወሰን

1. መመሪያው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተብለው በተመለከቱት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

2. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚሸጡዋቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ተጠቃሚ በሆኑ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ነው።

3. ይህ መመሪያ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ አንድ የሥራ ሂደት/ክፍል ለሌላው የሚያቀርበው ዕቃና የሚሰጠውን አገልግሎት አይመለከትም::

5. አጠቃላይ ፖሊሲ እና መርሆዎች

1. መርህ

የዚህ መመሪያ መርህ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ክፍያ አቅርቦትና ፍላጎት የገበያ ስርዓትን እንዲከተል በማድረግ የሃብት አጠቃቀም ማሣደግ ነው::

2. ፖሊሲ

ሀ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያቀርቡት ዕቃና አገልግሎት ወጪ የሚሸፈነው ተጠቃሚ በሆኑት የሕብረተሰብ ክፍል ነው:: የክፍያው መጠንም በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወሰን የፖሊሲ ውሣኔ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል::

ለ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት ዕቃ እና አገልግሎት የሚያስፈልገው የወጪ ጫና በአጠቃላይ የግብር ከፋይ ኅብረተሰብ ላይ ከሚያርፍ ይልቅ የዕቃው እና የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ የሚያርፍበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው::

6. የክፍያ ተመን ዕቅድ ስለማውጣትና በየጊዜው ስለሚታይበት ሁኔታ

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በስራ ላይ ካሉ የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎች በመሰብሰብ ላይ የሚገኙትን የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ባህርይ፣ የሥርጭት አድማስ ደረጃ፣ በቂነት እና ተገቢነት በሚመለከት ቢሮው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ማሳወቅ ወይም ማቅረብ፣

2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አዲስ ክፍያ የሚተመንላቸው እና ማሻሻያ የሚደረግባቸውን የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን የሥርጭት አድማስ እና በሥራ

ላይ መዋል መቻላቸውን እንዲሁም የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን መጠን የውሣኔ ሐሣብ ማቅረብ አለባቸው፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውሣኔ ሃሣብ ለማቅረብ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

ሀ. እያንዳንዱን ዕቃ ለማቅረብና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገውን ወጪ በሚመለከት ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ መጠቀም፣

ለ. መሥሪያ ቤቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ክፍያ የሚጠየቅበትን ዕቃና አገልግሎት በቀላሉ እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለማወቅ እንዲሁም በዕቃውና በአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሚሆነው እያንዳንዱ ሰው በአገልግሎቱ በምን ያህል መጠን እንደሚጠቀም ለማወቅ የሚችል መሆኑን፣

ሐ. በዕቃውና በአገልግሎቱ ላይ ክፍያ መተመን ክፍያው በተተመነበት ጊዜና ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ጨምሮ ክፍያው ገቢ በማመንጨት ረገድ ያለውን አቅም፣

መ. ከዋጋው፣ ዕቃውና አገልግሎቱ ካለው የጥራት ደረጃ፣ ከተጠቃሚው ፍላጎት እና ዕቃውና አገልግሎቱ የተጠቃሚውን ፍላጎት በማሟላት ረገድ ካለው ብቃት አንፃር ተጠቃሚው ለዕቃውና ለአገልግሎቱ የሚጠየቀውን ዋጋ ለመክፈል ያለውን አቅም፣ እና

ሠ. ለአስተዳደር ቀላል መሆኑን እና የዕቃና የአገልግሎት ክፍያውን ለመሰብሰብ የሚደረገውን ወጪ ከግምት ውስጥ ማስገባት፡፡

3. ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፡-

ሀ. ለንብረተሰቡ ከሚያቀርቡት ዕቃና ከሚሰጡት አገልግሎት ውስጥ ክፍያ የማይጠየቅባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚመለከት ክፍያ እንዲጠየቅ ቢደረግ በሥራ ላይ መዋል ስለመቻሉ፣ ስለአስፈላጊነቱ ግምገማና ጥናት ማካሄድ፣

ለ. የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ለማስከፈል መሥሪያ ቤቱ አዲስ የሕግ ሥልጣን ያስፈልገው እንደሆነ ማጣራት፣

ሐ. ማንኛውም የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል የሚችሉት በዚህ መመሪያ በተገለፀው አኳኋን የውሣኔ ሃሣብ ለቢሮው አቅርቦ የመስተዳድር ምክር ቤት ሲፈቅድ ብቻ መሆኑን፣

የሚሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

7. የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ዕቅድ ስለመንደፍ

1. የመስተዳድር ምክር ቤት ወይም የክልል ምክር ቤት፣ በሕግ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ ወይም በፖሊሲ ምክንያቶች በተለየ ሁኔታ እንደአስፈላጊነቱ እንዲፈፀም ካልወሰኑ በስተቀር በመርህ ደረጃ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎትና ለሚያቀርቡት ዕቃ የሚደረገውን ወጪ በቀጥታ የዕቃውና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆነው የሕብረተሰብ ክፍል መሸፈን አለበት።

2. በመንግሥት የሚደረገውን ድጎማ ደረጃ በደረጃ ለማስቀረት እንዲቻል ወጪው በዕቃና በአገልግሎት ክፍያ መልክ ሊተካ የሚችልበት በግልጽ የሚታወቅ ዕቅድ ሊኖር የሚገባ ሲሆን፣ የዕቃና የአገልግሎት ክፍያው መጠን ወጪውን ለመሸፈን ከተዘረጋው የክፍያ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

3. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በአንቀጽ 6 በተመለከተው መሠረት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን እንደገና በሚያዩበት ጊዜ ለእያንዳንዱ አገልግሎት በአማራጭነት የተወሰደውን ወጪን ለመሸፈን የሚያስችለውን ዕቅድ በሚመለከት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ እና ይህ ዕቅድ የተመረጠበትን ምክንያት ማስረዳት አለባቸው።

4. የመስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳብ የቀረበበትን ወይም ሌላ ለዕቃና ለአገልግሎት የተደረገውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ዕቅድ ካፀደቀ፣ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር በተከታታይ ማሻሻያዎች የዕቃና የአገልግሎት ክፍያው መጠን በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከቀረቡት ወጪን

የመሸፈን ዕቅድ ቢሮው በደገፈው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት በማድረግ ይወሰናል።

5. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ የውሣኔ ሃሣብ በቢሮው ተደግፎ ቀርቦ ቢመስተዳድር ምክር ቤት በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ከዕቃና ከአገልግሎት ክፍያ የሚገኘው ገቢ ዕቃውን ለማቅረብ እና አገልግሎቱን ለመስጠት ከተደረገው ወጪ በላይ እንዲሆን በሚያስችል ሁኔታ ክፍያ ሊጣል አይችልም።

8. ክፍያ እንደገና የሚታይበት የጊዜ ሠሌዳ

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በየዓመቱ ወይም ቢሮው በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን እንደገና ማየት እና ያወጡትን ወጪና የሚያስከፍሉትን ክፍያ የሚገልጽ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው። ይህንን በተመለከተ ቢሮው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ሊጠይቅ ይችላል።

9. መጽደቅ

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አዳዲስ የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን እና በነባር ክፍያዎች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ለውጥ በሚመለከት ያላቸው የውሳኔ ሃሳብ በቢሮው በኩል ለመስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ ማድረግ አለባቸው።

2. ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ የራሱን አስተያየት ሊያክል ይችላል።

3. ከላይ በአንቀጽ 9/1 የተጠቀሰው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሕብረተሰቡ የሚያቀርቡት ዕቃና የሚሰጡት አገልግሎት በመደበኛነት የሚከናወን ካልሆነ ወይም ለዕቃው እና ለአገልግሎቱ የሚጠየቀው የተናጠል ዋጋ ከብር 50.00 /ሃምሣ ብር/ የማይበልጥ ከሆነ የክፍያው ልክ ለቢሮው በማቅረብ ሊያፀድቁ ይችላሉ።

10. የዕቃዎችንና የአገልግሎቶችን ደረጃ ስለመወሰን

1. አዳዲስ የዕቃ እና የአገልግሎት ክፍያዎችን መወሰን ሲያስፈልግ መጀመሪያ የዕቃና የአገልግሎት ክፍያው ደረጃ የሚወሰንበትን መመዘኛ ዎች ማውጣት ያስፈልጋል::

2. የዕቃውና የአገልግሎቱ ተፈጻሚነት አድማስ እና ደረጃ በሕግ የተወሰነ ሲሆን፣ የሚመለከተው በተጠቀሰው ሕግ ላይ የተዘረዘሩት መሠረተ ሐሣቦች ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ::

3. የዕቃውና የአገልግሎቱ ተፈጻሚነት አድማስ እና ደረጃ በሕግ ያልተወሰነ ሲሆን፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከዚህ በታች በተመለከተው ይመራሉ::

   ሀ. ዕቃውና አገልግሎቱ ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሌሎች ተግባራት እና አገልግሎቶች በቀላሉ ሊለይ እና ሊታወቅ የሚችል ራሱን የቻለ ተግባር ወይም እንቅስቃሴ መሆኑ፣

   ለ. እያንዳንዱ ተጠቃሚ ያገኘው ዕቃና አገልግሎት መጠን ተለይቶ ሊመዘገብ እና ሊለካ የሚችል መሆኑ፣

   ሐ. የዕቃውና የአገልግሎቱ ባህርይ እያንዳንዱ ተጠቃሚ ባገኘው አገልግሎት መጠን ክፍያ መጠየቅ፣

   መ. በወጪ ስሌቱ መሠረት ዕቃውንና አገልግሎቱን ለመስጠት በተደረገው ወጪ ላይ ብቻ የተመሠረተ ሲሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለሌሎች ተግባራትና አገልግሎቶች ከሚደረገው ወጪ የሚለይ መሆኑ፣

   ሠ. ለአንድ ዓይነት ዕቃና አገልግሎት በጥራት ደረጃው የተለያየ ክፍያ መጠየቅ የሚቻልበት መንገድ መፈለግ፣ እና

ረ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያላቸው የአቅም ውሱንነት ሊሰጡ በሚችሉት ዕቃና አገልግሎት ብዛት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው::

11. በወጪ መጠን ላይ ጫና ያላቸው ሁኔታዎችና ወጪን ማስላት

1. የዕቃና አገልግሎት ክፍያ ዕቅድ እና የክፍያ ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ወይም የሚደረግ ቢሆንም በመርህ ደረጃ ዕቃውን ለማቅረብና አገልግሎቱን ለመስጠት የተደረገው ሙሉ ኢኮኖሚያዊ ወጪ መታወቅ ይኖርበታል::

2. ዕቃውን ከማቅረብና አገልግሎቱን ከመስጠት ጋር በተያያዘ የተደረገውን ቀጥተኛ ወጪ እና ከመሥሪያ ቤቱ ጠቅላላ ወጪ ውስጥ እነዚህን ተግባራት ለመደገፍ የተከናወኑ ተግባራት ድርሻ የሆነውን ቀጥተኛ ያልሆነ ወጪን ይጨምራል::

3. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለዕቃውና ለአገልግሎቱ የሚደረገውን የወጪ ግምት በሚሠሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ጨምረው ማሰብ ይኖርባቸዋል::

ሀ. በወቅቱ ባለው የወጪ መጠን ላይ ጭማሪን ወይም ቅናሽን ሊያስከትሉ የሚችሉ እንደ ቴሌፎን እና ፖስታ አገልግሎት የመሳሰሉትን ክፍያ ላይ ለውጥ እንደሚደረግ በማስታወቂያ ከተገለፀ እና በክፍያ ላይ በሚደረግ ድርድር ተቀባይነት ያገኘ የክፍያ መጠን፣

ለ. የወጪ ግምት ዕቃውን ለማቅረብና አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊ በሆኑ ዕቃዎች ላይ ሊያጋጥም የሚችለውን የዋጋ ውጣ ውረድ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን የሚቻል እስከሆነ ድረስ የአገልግሎቱን የወጪ መሠረት የሚያሳይ የዋጋ አመልካች እንዲኖር

ማደረግ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ይህንን በሚመለከት ከቢዩሙ ምክር ማግኘት እንደሚችሉ፣

ሐ. ለዕቃውና ለአገልግሎቱ ይኖራል ተብሎ በሚገመተው ፍላጎት ምክንያት አገልግሎቱን ለመስጠት ወይም ለማሠራጨት የሚደረገው ወጪ መጨመር ወይም መቀነስ ለውሳኔ የቀረበውን የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

12. አገልግሎቱ የሚኖረውን ተፈላጊነት ስለመገመት

1. በዕቃና አገልግሎት ላይ ከተተመነው ክፍያ መጠን እንዲሁም ከሚሰጠው ዕቃና አገልግሎት ጥራት በተጨማሪ ተጠቃሚዎች ለአንድ ዕቃና ለአንድ አገልግሎት ለመክፈል የሚችሉትን ዋጋ የሚወስኑ ሌሎች ሁኔታዎች ማወቅ ይኖርባቸዋል።

2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዕቃና አገልግሎት ክፍያ ላይ ጭማሪ ቢደረግ በፍላጎት መጠን በመንግሥት ገቢ መጠን ላይ የሚኖረውን ውጤት መገመት ሲፈልጉ፣ ወጪን ለመሸፈን የሚያስችለውን ዕቅድና በሥራ ላይ ሊውል የሚገባውን የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ መጠን በሚመለከት የውሳኔ ሃሳብ ሲያዘጋጁ የሚከተሉትን በጥንቃቄ ማየት አለባቸው።

ሀ. ባለፉት ጊዜያት ለዕቃውና ለአገልግሎቱ የነበረው ፍላጎት የተከተለው አቅጣጫ እና አቅጣጫውን በማስያዝ ረገድ ወሳኝነት የነበራቸውን ሁኔታዎች፣

ለ በዕቃውና በአገልግሎቱ ክፍያ ላይ ጭማሪ ቢደረግ ወይም አዲስ ክፍያ ቢጣል የተጠቃሚዎችን የመክፈል አቅም ጨምሮ በተጠቃሚዎች የፍላጎት መጠን ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉትን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች፣

ሐ. የአገልግሎቱ የወቅቱ ጥራትና ብቃት ደረጃ በዕቃውና በአገልግሎቱ ክፍያ መጠን ላይ ጭማሪ ቢደረግ ወይም አዲስ ክፍያ ቢጣል በተጠቃሚዎች የመክፈል ፈቃደኝነት እና የመክፈል ችሎታ ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ፣

3. በአጠቃላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወጪን ለመሸፈን የሚያስችልን ዕቅድ በሚመለከት የውሳኔ ሃሳብ ሲያዘጋጁ በሌሎች የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ በመንግሥት የፍላጎት ቅደም ተከተል ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

13. ለሕዝብ ስለማስተዋወቅ፣

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ አዳዲስ፣ የተሻሻሉና ነባር የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ዝርዝር በሥራ ላይ የሚውሉበትን ቀን ጭምር ሕዝብ እንዲያውቅ ማድረግ አለባቸው። የተደረጉ ለውጦች የዕቃውና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ለተቋቋሙ ድርጅቶች መላክን ጨምሮ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች እንዲሁም በሌሎች መንገዶች በስፋት እንዲሰራጭ መደረግ ይኖርበታል።

14. የዕቃና አገልግሎት ወጪን የመተመን ዘዴ

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ የውሣኔ ሃሣብ ለማቅረብ መከተል ያለባቸውን ወጪን የመተመን ወይም የማስላት ዘዴ እና ሌሎች ማብራሪያዎች በተመለከተ ቢቢሙ በሚያወጣው የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ማንዋል በዝርዝር ተካቶ ከዚህ መመሪያ ጋር በተጓዳኝነት ተፈጻሚ ይሆናል።

15. የተሻረ መመሪያ

ከዚህ ቀደም የነበረው "የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 8/1996" ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

15. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከየካቲት 1/2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር

አየነው በላይ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ